# <u>ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2017 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

በዲሴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ፣ ነፋሻማና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተስተውሎ ነበር። በተለይም በመካከለኛው፣ በምሥራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ይበልጥ ቅዝቃዜው ያየለ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ለተከታታይ ቀናት ከ5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በቢሾፍቱ -7.6፣ -5.0፣ -3.0 እና-0.8፣ በሐሮማያ -3.2፣ -2.4፣ -1.6 እና -0.4፣ በደብረብርሀን -4.0፣-1.8፣-2.8 እና-1.6፣ በአርሲሮቤ -1.5፣ በመሀል ሜዳ -1.5 እና -2.0፣ በአዲግራት -1.0፣ በወገል ጤና -0.5 እና -2.4፣ በእምድብር 3.1፣ በጃራ 1.8፣ በክብረመንግስት 3.9፣ በኮፈሌ 2.8፣ በማይጨው 1.8፣ ፣ በናዝሬት 4.4፣ በሰንቃጣ 4.0፣ በሴሩ 4.0፣ በሾላ ገበያ 1.2፣ በየትኖራ 3.0፣ በኮምቦልቻ 1.6፣ በጂማ 2.0፣ በመተሀራ 3.4፣ በሮቤ 1.2፣ በአዴሌ 1.2፣ በአድዋ 2.0፣ በአይደር 2.0፣ በአዲስ አበባ ቦሌ ኢንጂነሪንግ 1.2፣ በአምባማርያም 1.5፣ በአፅቢ 2.0፣ በባቲ -2.6 እና -2.4፣ በቦሬ -3.0፣ በጨፋ 2.3፣ በዳንግላ 4.0፣ በደባርቅ 3.5፣ በእነዋሬ 1.5፣ በፍቼ 2.8፣ በወረኢሉ 3.8 እንዲሁም በሆሳዕና 4.0 በዲግሪ ሴልሸየስ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅና ፀሐያማ አየር ሁኔታ ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ከአየር ሁኔታ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1፣2 እና 3) ፡፡

ካርታ1   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



## ካርታ2   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



## ካርታ3   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ከመደበኛ በታች          መደበኛ          ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው  ተጽዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በተጨማሪ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በመሆኑ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ በአርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና በተለያዩ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አኳያም ሆነ በመጠጥ ውሃና በግጦሽ ሳር አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደነበረው ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የተስተዋለው የሌሊትና የማለዳው ቀዝቃዜ በእንሰሳት ላይ በጓሮ አትክልትና በፍራፍሬዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከዲሰምበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ ከዲሰምበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በሀገሪቱ ባሉ በሁሉም ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2017 በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## <u>እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2017 የሚኖረው</u>
## <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በሰሜን ንፍቀ ክበብ ከሚገኘው ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

በዚሁ መሰረት <u>በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የአገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ እንደሚቆይና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንዳለፉት ቀናት ሁሉ ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ሁኔታ ሊቀጥል እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ ቀስ በቀስ በአንዳንድ የመካከለኛው፣ የምስራቅና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡</u>

## <u>እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ</u>

በሚቀጥለው የዲሴምበር ወር ሶስተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው የሚቆይበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የክረምት ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የበጋ ወቅታቸው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን የሚያካሂዱበት ጊዜ በመሆኑ የሚጠበቀው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ በተለይም በሃገሪቱ ከፍተኛ ቦታወችና ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንዳለፉት ቀናት እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት አንዳንድ እድገታቸውን ባልጨረሱና በመስኖ በተዘሩ በጓሮ አትክልቶችና በቋሚ ተክሎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከዲሰምበር 21-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>

## <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

ከለይ በተሰጠዉ ትንበያ መሠረት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚቀጥልና የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚሁ መሰረት በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያል፡፡